**27.07.2018**

# ቃል-ኪዳን! ከማን ጋር?

የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በተመለከተ በሓምሌ ወር የምንሰማው ዜና የሚያስደንቅ ፍጥነት ያለው ነው። ለዚሁም ግንኘቱ ምን ያህል ጥልቀትና ዕድሜ ሊኖሮው ይችላል፡ ብሎ መጠየቅ ኣስፈላጊ ይመስለኛል።

ለመሆኑ ኣዲስ ጋብቻ ብለን እንጥራው ወይም ሁለተኛ?

በበለጸጉ ኣገሮች ልጅን እንኳን ለትምህርት - በትምህር-ቤት - ከማስገባታቸው በፊት ምን ያህል ጥረትና ግዜ እንደሚስፈልጋቸው እንታዘባለን። የሚገርመው ለብዙ ሺ ህዝብ የህይወት መጥፋትና ጠንቅ የሆነው ከሃያ ዓመት በፊት የተጀመረው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት ኣሁን የምንሰማውን ያህል ፍጥነት የነበረው መሆኑን ኣስታውሳለሁ።

የማያከራክር እውነት፡ የሁለቱ ኣገሮች ህዝቦች በባህልም በትውልድም ያላቸው መቀራረብ ነው። ኣሁን ለሚታቀድ ግንኙነት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ወሳኝ ሊሆኑ ግን ኣይችሉም። ወሳኙ የህዝቦች ኣመለካከትና ፍላጎት መሰረት ያደረገ፣ በህግ ባለሞያዎች የተጠና፣ በሕዝብ ተወካዮች የጸደቅና የሚከበር፣ ውል ሲኖር ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፤ በበለጸጉ ኣገሮች ወላጆችና ልጆች የጋራ-ንበረት ወይም የጋራ ድርጅት ሲነራቸው፣ ፍርድ-ቤት የሚያውቀው ውል ይኖራቸዋል። ውል ኣለማክበር የሚያስከትለው ኪሳራም ግልጽ ይደረግላቸዋል።

በ**1961** ዓ.ም.ፈ የተጀመረው የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ጠንቅም፡ ኣጼ-ሃይለስላሴ የፈደረሽን ውል እንዲፈርስ ማድረጋቸው መሆኑን በቅርብ የተከታተሉት ፕሮፈሶር በረከት ሃብተስላሴና ሻለቃ ዳዊት ወልደገርጊስ ይገልጹታል። ለዚሁም የጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ኣቢይና የፕረሲዳንት ኢሰያስ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጉብኝቶችና ንግግሮች በጥልቅ መገምገም ኣስፈላጊ ነው።

የክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ የኣስመራን ጉብኝት ከልብ ነው የምደግፈው። ዕጣችን የስሃራ በረሃና የሜዲተራንያን ባህር ነው ለሚሉ ልጆቻችንም የተስፋ ጩራን ነው። ለክቡር ጠቅላይ ሚንስትር በከተማው የተደረገው ደማቅ ኣቀባበል ሰምተናል። በክፍለ ዓለማችን ደማቅ ኣቀባበል መገምገም ቀላል ኣይደለም። በቀበሌ ተገደህም እንግዳ መቀበል የተለመደ ሰለሆነም ነውና።

የክቡር ኣቶ ኢሰያስ የኢትዮጵያ ጉብኝት በተመለከተ የኣዋሳ ከተማ ንግግራቸውም ክብርና ፕረቶኮል ያልጠበቀ መኖሩን ለመገንዘብ ችያለሁ። ለክቡር ዶክተር ኣቢይ፡- "ከዛሬ ጀምሮ የምትመራን ኣንተ ነህ"፣ ስልጣን ኣስረክቤህ ኣለሁ"፣ የሚል ኣነጋገር፡ ስልጣኑ ራሳቸው የነጠቁት እንጂ የኤርትራ ህዝብ እንዳልሰጣቸው ያመለክታል። የቈሳቊስ ስጦታ እንጂ የፕረሲደንትነት ስጦታ ማስረከብ ከሳቸው ብቻ ነው የሚሰማ።

ክቡር ኣቶ ኢሰያስ በኣመሪካ ኣገር የስራ ጉብኝት ባደረጉት ወቅትም ከኣመሪካ ድምጽ-ረድዮ **(VOA)** ለቃለ-መጠይቅ ቀርበው ጋዜጠኛው፡ በኤርትራ የፕረሲዳንት ምርጫ መቼ ይደረጋል፣ ብሎ ሲጠይቃቸው፡- "ለኔ ስልጣኑ በኮንትራት የሰጠኝ የለም" የሚል ቃል መስጠታቸው ይታወሳል። የሓምሌ ወር የኣዲስ ኣበባ ንግግራቸውም፣ "እርጋታችን በመሸበርና ልማትና እድገታችን ለመውደም፡ ለማንም ቢሆን ኣንፈቅድም" የሚል ነበር። ኣሁንም ቢሆን ለሁለቱም ኣገሮች ህዝቦች ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ፡ ለሰላም፣ ለድርድርና ለጋራ ጥቅም መጠበቅና ማስከበር የሚል ኣስተሳሰብ፡ ከሳቸው የራቀ ይመስላል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ከሁሉም የኣገሪቱ ተወካዮች፡ ከኢንቨስትሜንቱ እቅድ ባሻገር በእኩልነትና በመከባበር መልካም ጉርብትና እንዲኖር፡ ረጋ ብሎ የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት መፈተሽ፡ በጣም ኣስፈላጊ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በኔ ኣመለካከት፡ ክቡር ኣቶ ኢሰያስ ችላ ቢሉትም፡ የኣገሮቹ ድንበር ጥያቄ መመለስ ለጓደኝነትና ኣብሮ ለመስራት ይበጃል ባይ ነኝ። የቀድሞ የግድ ጋብቻ፡ ውጤቱ ድህነትና ሞት መሆኑን ኣይተነዋል። የዓይን ምስክሮችም ነን። የኤርትራ ህዝብም ኣሁን ድርሻው ካላበረከተ፣ የጋዜጠኛው በዓሉ ግርማ መጽሓፍ "ኦሮማይ" ማንበብ ኣይጠቅመውም። ኣዲስ ቢጻፍም ኣንባቢ ኣያገኝም።

ሞገስ ሃብተማርያም
ጀርመን